# ምርጫውም ተጭበረበረ ፣ ኢ.ህአዴግም አሸነፍኩ አለ ፣ እኛንስ ምን ይበጀን ይሆን ?

ከግንቦት ስምንቱ ምርጫ ወዲህ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ ልዩ መልክና አቅጣጫ ይዞ ይገኛል። በአንድ በኩል እስከ አፍ ጢሙ ድረስ የታጠቀ ፣ ደም የጠማውና ስልጣን ወይም ሞት ብሎ ቆርጦ የተነሳ የወያኔ/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው የኢ.ትዮጵያ ህዝብና የተቃዋሚ ኃይሎች ተፋጠው ይገኛሉ። ትግሉ በአንድ በኩል የህዝብን ውሳኔና የነፃነት ጥም ረግጦ በያዘና ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ነፃነትን ፣ ዲሞክራሲያዊ ህይወትንና የሰላምን አርማ አንግቦ ይዞ ስልጣኔና ዕድገትን እፈልጋለሁ ብሎ በተነሳው ሰፊው የኢ.ትዮጵያ ህዝቦች መሀከል ነው። የወያኔ/ኢ.ህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ግትርና እልህ በተሞላበት አቋሙና ባህርዩ የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ከረሀብ ፣ ከድህነትና ከጨለማ አገዛዝ መላቀቅ የለበትም ብሎ ቆርጦ ሲነሳ ፣ ሰፊው የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ከእንግዲህ ወዲያ የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ ማሽከርከር አይቻልም ፤ በዚህ ዐይነት አገዛዝ ውስጥ አንገታችንን ደፍተን መገዛትና መኖር አንችልም ብለው በመነሳት ለእነ አቶ መለስ/ በረከት ሰመኦን አምባገነናዊ አገዛዝ የራስ ምታት ሆነውበታል።

ከምርጫው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የተካሄደውን ቅንጅትንና ህብረትን የሚደግፈውን ሰለማዊ ሰልፍና የምርጫውን ሂደትና ውጤት ስንመለከት ፣ ሁለቱም ድርጊቶች ለተራ የአገዛዝ ለውጥ የተደረጉ ክንዋኔዎች እንዳልነበሩ መገንዘቡ እጅግ አስፈላጊ ነው። የኢ.ትዮጵያ ህዝቦች በሰላማዊ ሰልፉም ሆነ በምርጫው ያሳዩትና ያረጋገጡት አስራ አራት ዐመት ያህል ከውጭ ኃይሎች ጋር በመመሰጣጠር ኢ.ትዮጵያን በድህነት ያስተዋወቃትን ፀረ-ዲሞክራሲያዊና ፀረ-ነፃነት ኃይል ከጫንቃቸው ተሸቀንጥሮ ዕውነተኛ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ህይወት ለመጎናፀፍ ነው። በተጨማሪም የግንቦቱ ስምንት ምርጫ ያረጋገጠው ፣ እዚህ ምዕራብ አውሮፓ ውስጥ እንደምናየው አንዱን ፓርቲ በሌላ በመተካትና የተወሰኑ የህብረተሰቡን ኑሮ የማይለውጡና የአገሪቱን መሰረታዊ ችግሮች የማይፈታ አካሄድ ከአራት ዐመት በኋላ ህብረተሰቡን ለሌላ ምርጫ ለማዘጋጀት እንደሚደረገው ዐይነት ሳይሆን ፣ የመንግስቱን መኪና ከዳር እስከዳር ተለውጦ በአዲስ ዲሞክራሲያዊና የሰለጠነ አሰራር በመተካት የኢ.ትዮጵያ ህዝቦች ዕውነተኛ ነፃነትን እንዲጎናጸፉ ለማድረግ ነው። በዚህም መሰረት ህዝባዊ ባህርይ ያለው አገዛዝና መንግስት ተቋቁሞ ሰፊው ህዝብ ከዳር እስከዳር በመንቀሳቀስ የስልጣኔና የነፃነት ባለቤት እንዲሆን ለማረጋገጥ ነው። አገዛዙም ሆነ መን ግስታዊ መኪና በውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በመውደቅ በዓለም አቀፍ ኢ.ንስቲቱሽኖችና የምዕራብ መንግስታት እየተጠመዘዘና የድህነቱንና የረሀቡን ዘመን እንዲያራዝሙ ለማድረግ አይለም። ስለሆነም የግንቦቱ ምርጫ መልዕክት ብሄራዊ ነፃነቷን ያስጠበቀች ፣ በዲሞክራሲያዊና በእኩልነት መርሆች ላይ የተመሰረተ አንድነቷ የሚረጋገጥበት ፣ የበለጸገችና የጠነከረች ኢ.ትዮጵያ በአፍሪቃ ምድር ብቅ ብላ እንደትወጣና ለሌሎችም ጭቁን የአፍሪቃ ህዝቦች ምሳሌ እንድትሆን ነው። የግንቦቱ ምርጫ መልዕክትና የህዝባችን ፍላጎት ከዚህ ያነሰ አይደለም።

የዛሬ አስራ አራት ዐመት ወያኔ በሻቢያና በሲአይኤ እየታገዘ ግዙፍ እየተባለ የሚጠራውን የደርግ ሰራዊት "ሲገረስስ" ፣ በደርግ አገዛዝ ሲንገሸገሸ የከረመው ህዝባችን እፎይታን ለጊዜው ያገኘ ቢመስልም ከበስተጀርባው የተጠነሰሰው ሴራ ይፋ ወጥቶ እን ዳረጋገጠው ህብረተሰባችንን ዘላለማዊ ቀውስ ውስጥ ለመክተት እንደነበር ሁኔታውን በጥብቅ የተከታተለ ሊገነዘብ ይችላል። በአስራ አራት ዐመት የወያኔ/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ አንዳንዶቻችን ግራ በመጋባትም ሆነ እራሳችንን ከሁኔታው ጋር ለማቀናጀት አንድ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ውስጥ ለመድረስ አሰቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የወደቅን ኃይሎች ጥቂት አልነበርንም። በተለይም የወያኔ/ ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ከምዕራቡ ዓለም ያገኝ የነበረው ድጋፍና አገራችንን የነሱ መጨፈሪያ ማድረግ ለብሄራዊ ነፃነት የምናደርገውን ትግል ለዘብ ያደረገና የትኛው መስመር ነው ትክክል ብለን የህዝባችንን የነፃነት ጥማት የሚያግዝ በሳይንሳዊ ጥናት የተደገፈ የፖለቲካ ስልት ይዘን በህዝባችን ላይ የሚፈጸመውን በደል በበቂው ለማስተጋባት ችግር ውስጥ ወድቀን እን

ደንበር የማይታበል ሀቅ ነው። በመጀመሪያ የወያኔ/ ኢህአዴግ አገዛዝ ለምን በተለይም በአሜሪካንና በእንግሊዝ ተደግፎ ስልጣን በመያዝ እንደዚህ ዐይነት ፖለቲካ ማካሄድ ቻለ? የሚለውን አመለካከት ወደ ውጭ አውጥተን ለመከራከር አልቻልንም። በምዕራቡ ዓለም ፣ በተለይም በአሜሪካን ላይ ያለን የፖለቲካ አመለካከት ልዩ ስለሆነ ፣ የወያኔን ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚውጠነጠነውና ድህነትንና ጦርነትን ከሚፈለፍለው የተቀነባበረ ፣ ለብዞዎቻችን በግልጽ የማይታይ ፖለቲካ ጋር በማጣመር ትግላችንን የጠራ መልክ ለመስጠትና ህዝባችን እንዲገነዘበው በቂ ሙከራ አልተደረገም። ብዞዎቻችን በምዕራቡ ዓለም ዲሞክራሲ የሰፈነ ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያበበ ስለሆነ ፣የምዕራብ መንግስታትና ኢንስቲቱሽኖቻቸው የኛን ዕድገትና ብልጽግና እንደሚሹ አድርገን በመመልከታችን ትግላችን ጥራት እንዳይኖረውና ህዝባችን አስራ አራት ዐመት ያህል ግፍ እንዲፈጸምበት የትግሉ መስመርና አቅጣጫ ሳይንሳዊ መልክ እንዳይኖረው አድርገናል ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። እንደዚህ ዐይነቱ ለዘብተኛ አቋምና ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሄደቶችን ስትራቴጂያዊ በሆነ መልክ ለመመልከት ያለመቻል ወይም ደግሞ ያለመፈለግ በታሪክ ውስጥ እንደታየው የብዙ ህዝቦችን ትግል አጨናግፎ ዛሬ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ የሚሰቃይበት ከተሳሳተ የፖለቲካ ፓራዲግማና ሳይንሳዊ አመለካከት የመነጨ ነው።

በዚህም መሰረት ወያኔ/ኢህአዴግ የዛሬ አስራ አራት ዐመት ስልጣን ለመያዝ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ ለብዙዎቻችን ግልጽ ያልሆኑ ዓለም አቀፋዊ ፖለቲካዎች ነበሩ። ሰለጠንኩ የሚለው የምዕራቡ ዓለም ይጠባበቅ የነበረው ልዩ ሁኔታ ነበር። በአስራ ሰባት ዐመት የደርግ አገዛዝ ሲሰቃይ ለነበረው ህዝባችን ዲሞክራሲያዊ ህይወትንና ሰላምን ለማጎናፀፍ አልነበረም። ይጠባበቁት የነበረው ፣ ኢትዮጵያ በጎሳ የተከፋፈለች አገር እንደመሆኗና ምሁሩም ተሚጦ ስላለቀ ህዝቡ አይ በዚህ በአንድ ጎሳ በሚመራ ኃይል ላይ በመነሳት አገሪቱ ወደ እርስ በርስ ጦርነት ታማራለች። ካሊያም የሃይማኖት ጦርነት በመከሰት ትርምስ ይፈጠራል የሚል ነበር። በዚህም አማካይነት ኢትዮጵያን እጅግ በተግማማው የተባበሩት መንግስታት ቁጥጥር ስር በማድረግ የፖለቲካውን ሂደት ለመቆጣጠርና አገሪቱ በድህነት እን ድትቀጥል ለማድረግ ነበር። በሳሉ ህዝባችን ግን ለዚህ የምዕራቡ ተንኮል ፍንጭ ሳይሰጥና ሁኔታዎችን ሳያመቻች ወደፊት መጓዝ ነበረበት። የምዕራቡን ዓለም ፣ በተለይም ደግሞ አሜሪካንን የገረመው ይህ የህዝባችን ዝምተኛነትና ዲሲፕሊንነት ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያን በጎሳ ከፋፍሎ ወደ አጠቃላይ የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መክተት እንደማይቻል የተገነዘበው አሜሪካ ፣ አገሪቱን በሀይማኖት ጦርነት ውስጥ መክተትና የአገራችንን ዕድል ለብዙ መቶ ዐመታት ማጨለም ፣ የድህነቱን ዘመን ማርዘምና ተመጽዋች ማድረግ ሆነ ስትራቴጂው። በአንዳንድ የምዕራብ መንግስታት መሪዎች ኢትዮጵያን የክርስቲያን አገር ብቻ አድርጎ ማስወራትና ከእስልምና ሀይማኖት የሚመጣባትን አደጋ መመከት እንዳለባት ፣ በዚህም በምዕራቡ የፀረ-እስላም እንቅስቃሴ ስትራቴጂዊ አትኩሮት ውስጥ ተካትታ በወንድማችን የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ላይ ለማስነሳት የተደረገው ሴራ ቀላል አልነበረም። በተለይም በአልቀይዳ "አቀነባባሪነት" በመስከረም አስራ አንዱ "የቴሮሪስቶች" ድርጊት ጦርነት ታወጀብኝ የሚለው የቡሽ/ቼኒ አገዛዝ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ደሀ አገሮችን በእዚህ ዓለም አቀፋዊ ጦርነት ውስጥ አካቶ የተለያየ ሀይማኖት የሚከተለውን ህዝባችንን አንድነቱን ጠብቆ ለዕድገት እንዳይነሳ ማደናቀፍ እንደ ዐላማ አድረጎ ያዘው።ህዝቡን ውዥንብር ውስጥ በመክተት በዋናው ችግሩ ላይ እንዳይረባረብ በማድረግ የትግሉን አቅጣጫ እንዲስት ለማድረግ ሞከረ። ለዚህም ካለምንም ማወላወል ለነጩ ዓለም የሚያጎበድደው የወያኔ /ኢህአዴግ አገዛዝ የአሜሪካንን ጥያቄ እምቢ ሳይል ኢትዮጵያም ዓለም አቀፍ ፀረ-አልቃይዳ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደምትሳተፍ አስታወቀ። ይህም ሁኔታ በዲሞክራሲ የሚታማውን የወያኔ አገዛዝ የምዕራቡ ዓለም ድጋፍ እንዲጎርፍለትና ጠቅላይ ሚኒስተር ብሌር በአቋቋሙት የአፍሪቃን ድህነት የሚያራዝም ኮሚሽን ውስጥ መካተትና ዕውቅነት ማግኘት የዚሁ ስትራቴጅ አንድ ገጽታ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ በእዚህ እንዳለ ወያኔ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድና በዓለም ባንክ ተቀነባብሮ በአገራችን ምድር የተካሄደው ጭንግፍ የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲና በተለይም ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ኤክስፐርቶች እየተጋበዙ እየመጡ የሚሰጡት የተሳሳተ ገለጻ ፣ በአንድ በኩል ለአቶ መለስ አገዛዝ ሌጂቲሜሲ ሲሰጠው ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የጎሳንና የዘረኝነትን ፖለቲካ የሚቃወመው ኃይል የትግሉን አድማስ ሰፋ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ስልጣኔ በአገራችን ምድር ውስጥ ከሚካሄደው ፖለቲካ በአሻገርና ለየት ያለ መሆኑን በሳይንሳዊ መነጽር በመመርመር ለህዝባችን ትክክለኛ አመራርን ለመስጠት አልቻለም። ይህ ጉዳይ ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከብሄራዊ ነፃነትና ከዲሞክራሲያዊ አንድነት ጋር አገናኝቶ የእነ አይኤም ኤፍን ፀረ-ሳይንሳዊና ፀረ-ህዝብ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መልክ ባለው መንገድ በመተንተን ሁለንታዊ ትግል ማካሄድ የትግሉ ዋና መሰረተ-ሃሳብ መሆኑ ለብዙዎቻችን ግልጽ አልነበረም። የኢህአዴግን የኢኮኖሚ ፖሊሲና በኢኮኖሚው ላይ ያለውን ቁጥጥር ላይ ከተዘረዘረው አመለካከት ውጭ ለማስቀመጥ ባለመሞከሩም ፣ ኢኮኖሚ ማለት ምን ማለት ነው ? ምን ዐይነት የኢኮኖሚ ዕድገትስ ነው አገራችን የሚያስፈልጋት ? ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት አሰቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ተገባ። ይህ የእነ አቶ መለስ ከውጭ ኃይሎች ጋር ተጣብቆ ርዳታን በማግኘት ህዝባችንን ማመስና በዚያውም መጠንም የአገሪቱ ኢኮኖሚ በፀና መሰረት ላይ ተዋቅሮ ሰፊው ህዝብ ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግና ከህብረተሰቡ ተነጥሎ የወጣ አገዛዝ በአለም አቀፍ የአገዛዝ ሰንሰለት ውስጥ ገብቶ በመሽከርከር ድህነትንና ረሀብን መፈልፈል የአገዛዙ ዋና መለዮ በመሆን የህብረተሰባችንን ችግር አጥፍና ድርብ አደረገው። ዝብርቅርቁ የገበያ ኢኮኖሚ አዲስ የፍጆታን አጠቃቀም ከማስፋፋት ባሻገር አገዛዙም ሆነ የውጭ ኃይል ተቀናቃኝ የፖለቲካ ኃይል ይወጣል ብለው አልገመቱም ማለት ይቻላል። አዲስ በተፈጠረው የህብረተሰብና የኢኮኖሚ ውቅር ፣ ህዝቡ በራሱ ችግር ስለሚወጠር የፖለቲካን ለውጥ አሰፈላጊነት ሊገነዘብ አይችልም ፤ ስለዚህም ያለውን አዲስ የህሊና ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ ተጠቅሞ የወያኔን/ኡህአዴግን አገዛዝ ማራዘም ይቻላል የሚል አጉል ግምት አደረባቸው። የህብረተሰቡ ኃይል ተሚጦ ያለቀና ከእንግዲህ ወዲያ ኢትዮጵያን እንዳሻው ማሽከርከር ይቻላል ብሎ የገመተው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝና ብሄራዊ-ነፃነታችንን ክፉኛ የሚቀናቀነው የውጭ ኃይል በአጭር ጊዜ ውስጥ ያልጠበቀው ሁኔታ ተከሰተበት። ኢህአዴግም እሱ የገመገመውን የፖለቲካ ሁኔታ ተጠቅሞ አምስት ዐመት ተደላድሎ የሚገዛ ስለመሰለው አገዛዙን እንደገና ለሌላ አምስት ዐመት በምርጫ ለማደላደል ዲሞክራት ነኝ ብሎ በመዘባነን ለወጭው ዓለም ለማረጋገጥ የግንቦቱ ምርጫ እንግሚካሄድ አበሰረ። ይሁንና ከሰላማዊ ሰልፍ በፊት የተካሄደው የፖለቲካ ክርክር ሁኔታው ለኢህአዴግ እንዳያመች አድርጎ ቀየረው። ኢህአዴግም ሆነ ብዙዎቻችን ያልጠበቅነው ሁኔታ ተከሰተ።

ከምርጫው በፊት የተካሄዱት የፖለቲካ ክርክሮች ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ሌላ አማራጭ አለ እኮ ? ብሎ ራሱን እንዲጠይቅና የጨለመው ተስፋው የፀሀይ ብርሃንን እን ዲያይና የአገራችን ዕድል ደብዛው እንዳልጠፋ ሊገነዘብ አስቻለው። የአስራ አራት ዐመቱ የኢህአዴግ እልክ አስጨራሽና የተመሰቃቀለ ፖለቲካ በህዝባችን ግንዛቤ ውስጥ እንዳለ ሆኖ ፣ የፖለቲካ ውይይቱ የማይናቅ አስተዋጽዎ እንዳበረከተ የማይታበል ሀቅ ነው። እን ደሚታወቀው ኢህአዴግ አንድን አገር አስተዳድራለሁ የሚል ፓርቲ ሊሰራና በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን(Legitimacy) ሊያሰገኝ የሚያስችለው ፖለቲካ ተግባራዊ ሲያደርግ አልታየም። ተግባራዊ ያደረጋቸው የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊና የሚሊታሪ ፖሊሲዎች በሙሉ ከህዝቡ ጋር ቅራኔ ውስጥ እየከተቱት እንደመጡና በፍጹም ህዝቡን ሊወክልና ኢትዮጵያን እንደ አንድ ነፃ አገር ጠንክራ እንድትወጣ የሚያደርጋት ፖለቲካዊ እርምጃዎች እንዳላካሄደ የኢትዮጵያ ህዝብ በበቂው ተግንዝቧል። የኢህአዴግም የፖለቲካ አደረጃጀት አንድ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ መደራጀት ባለበት መንፈስና የቲዎሪ መሰረት የተቀናጀ ባለመሆኑ አወቃቀሩ ሚሊታሪያዊና ድርጊቱም ከጫካ ይዞ በመጣው የማሸነፍ ፣ የማጥፋትና ጠላትን ማንበርከክ ወይም መደምሰስ በሚለው አስታሰሰብ ላይ የተገነባ ስለሆነ ፣ በአስራ አራት ዐመት ፖለቲካው ይህንን የጫካ ፖለቲካ ሲያራምድና እንዳንዱንም የህብረተሰብ ክፍል ሲያባልግ እንደቆየ ማንም የተገነዘበውና የለመደው ነው። የፓርቲው አመራርም ሆነ ካድሬዎቹ በአንዳች ዐይነት የፖለቲካ ፍልስፍናና ቲዎሪ የሚመሩ ሳይሆን የሚወስዱት

እርምጃዎች በሙሉ ግብዝነት የሚያጠቃውና ህዝብን የሚያተረማምስ ሆነ። ድርጅቱ በውስጡ በስራ ክፍፍል የዳበረና ህብረተሰብአዊ ችግሮችን ሊፈታ የሚያስችሉት መሳሪያዎች በፍጹም የሉትም። የድርጅቱ  የፖለቲካ ፍልስፍናና የቲዎሪ ድክመት ፣ እንዲሁም ደግሞ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን ለመፍታት ያለመቻል የግዴታ ማፍያዊ ወደ ሆነ ተግባር እን ዲሰማራ አደረጉት። የአገሪቱም ችግሮች በውጭ ርዳታና በነሱ ምክር የሚፈታ እንጂ በህዝቡ የማሰብ ኃይልና በምሁሩ ሊፈታ የሚችል መሆኑን በፍጽም ግንዛቤ ውስጥ ሊያሰገባ አልቻለም። እንዲያውም ከምሁሩና ከህዝቡ የሚመጡትን ምክሮችና ችግር ፈቺ መሳሪያዎች በማጣጣል የአገሪቱን ችግር ከውጭ በሚመጣ ርዳታ ብቻ ሊፈታ እንደሚችል ህዝቡን ለማሳመን መሯሯጥ ተያያዘ። እንደምናየው ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ መጠን የሌለው ርዳታ ወደ አገራችን ቢፈስምና የውጭ ኤክስፐርቶች እየመጡ ስለ አገራችን የኢኮኖሚ ችግር አፈታት በየጊዜው ገለጻ ቢያደርጉም የአገራችን ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ችግሮች እየተባባሱና እየተወሳሰቡ መጡ።

ይህ ፖለቲካዊ የፍልስፍና አልባነትንና የአገሪቱን ችግሮች በሳይንስ በተጠና ሳይሆን በእልህና በጉልበት ለመፍታት መሞከር ፣ የወያኔን/ኢህአዴግን መሪዎች ንጹህ የፊዩዳል ባህልና ከዚህ የመነጨ የሚሊታሪ አስተሳሰብ መታነጽ ያመለክታል። ድርጊታቸው ሁሉ በወረራና በማሸነፍ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ፣  ስልጣንን እንደ ህብረተሰብ ችግር መፍቻ ሊጠቀሙበት አልቻሉም። ባህርያቸው በፍጹም ሊፈቅድላቸው አልቻለም። በዚህም ላይ ፕላቶን ጂኦርጂያ በሚለው ጽሁፉ ላይ እንደሚያሰተምረን ፣ የእነ አቶ መለስ/በረከት ሰመኦን አስተሳሰብ እንደ ካሊክለስና ቱኪይዳይድስ -በግሪክ ለስልጣን መስገብገብና ለጦርነት የቆሙት ሶፊሰቶች- አገራችን ወንድማማችነትና ፍቅር የሚያብብባት አገር እንድትሆን ማድረግ ሳይሆን ፣ ለስልጣን መስገብገብና ጦርነት ማካሄድን ዋና ዓላማቻው በማድረግ ዘለዓለማዊ የህብረተሰብ ትርምስ መፍጠር ሆነ። ከዚህም ስንነሳ የእነ አቶ መለስ ዜናዊን አስተሳሰብ በዲሞክራሲያዊ ባህልና በውውይት አንጻለሁ ፤ የህብረተሰቡም አካል እንዲሆኑና ከህብረተሰቡ ጋር እንዲዋሃዱ አደራጋለሁ ማለት በፍጹም ዘበት ነው። ይህ እንደማይቻል አጠቃላዩን የአስራ አራት ዐመት የተንኮል ፖለቲካቸውን መመልከትና ብዙ መስዋዕትነት የጠየቁትን ትግሎች መገምገም እጅግ አስፈላጊ ነው።

እዚህ ላይ አንዳንድ ቀደም ብለው የተካሄደውን ፖለቲካና የተደረጉትን ትግሎችን መጥቀሱ እጅግ አስፈላጊ ነው።የወያኔ/ ኢህአዴግ የአስራ አራት ዐመት ፖለቲካ ሁለንታዊ መሆኑን መገንዘብ ያሰፈልጋል። ኢትዮጵያ የምትባለው አገር መለያ እንዳይኖራትና እራሷን እንዳትችል ከታች እስከላይ መበወዝ ነበረባት። ህብረተሰቡ እርስ በርሱ ከመበላላቱ ባሻገር ባህሉና ቋንቋው ተደምሰሶ ህዝቡ ማንነቱን መካድ አለበት ፤ የውጭ ተገዥ ሆኖ ድህነቱን አምኖ በተመጽዋችነት መኖር አለበት። ስለዚህም በግሎባላይዜሽን መዳፍ ስር በመውደቅ በተለይም አዲሱ ትውልድ ለብልሹ ባህል ሰለባ በመሆን ጭንቅላቱ መዞር አለበት። የማሰብ ኃይሉ መሟጠጥ አለበት። ነጭ እንደፈለገው የሚያሽከረክረው ዝቅተኛ ዜጋ በመሆን አገሩን መቸብቸብ አለበት። ይህ በአንግሎ አሜሪካን አማካይነት ተቀነባብሮ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚካሄደው በተለይም ታዳጊውን ትውልድ ለቆሻሻ ባህል ሰለባ ማድረግና ህሊናውን ማዳከም የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ሙያው በማድረግ በታሪካችን ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መልክ አዲስ አስከፊ ባህል በማዳበር ህብረተሰቡን ወደ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንደ ጣለው መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። በሌላ ወገን ግን እግዚአብሄር ሳይደግስ ሰውን አይጣላም እንሚባለው አነጋገር በቁጭት ከተለያየ አቅጣጫ ብሄራዊ ስሜትን ለማደስ የተደረገው ቆራጥ ትግል አዲስና ታታሪ ትውልድ እንዲበቅል አድርጎታል። ከየካቲቱ አብዮት ስህተት የተማረው እንደነ ቴዲ አፍሮ የመሳሰለው አዲስ ትውልድ ልዩ ዐይነት ውስጠ-ኃይል በማግኘት በሙዚቃ ፣ በስዕልና በኮሜዲ ያደረገው እምርታ ለህብረተሰባችን በሳል አስተሳሰብና ነገሮችን ማገናዘብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ማለት ይቻላል። በዚህ ላይ በተዘበራረቀ መልክም ቢሆን ከዚህም ከዚያም የሚጻፈው ጽሁፍ የህዝቡን አስተሳሰብ በመሰብሰብ ከተደገሰለት የእርስ በርስ መተላለቅ እንዲታቀብና የነገሮችን ሂደት በጥንቃቄ እን ዲመለከት አስችሎታል። እንደ ወያኔ መሪዎችና እንደ አሜሪካ ቢሆን ኑሮ ኢትዮጵያ አይ

ሌላዋ ዛየር ወይም ሃይቲ በመሆን ህብረተሰቡ በጦርነት ዘፍቆ ፍዳውን እያየ ይኖር ነበር። ይህ ግን አልሆነም። በዚህ ሁኔታ የተቃዋሚ ኃይሎች ቀስ በቀስ ተጠናክሮ መውጣት የህዝባችንን ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት አምጥቷል ማለት ይቻላል። በዚህ ዐይነት የተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ ነው እንግዲህ የግንቦቱ ስምንት ምርጫ የተካሄደውና ህዝባችን ድል በድል መሆን የቻለው።

ምርጫው ከተካሄደ ይኸው ወደ ሶስት ወር ተጠጋው። በአንድ አገር ውስጥ ምርጫ ተካሄዶ በአሸናፊነት የወጣው ኃይል ሳይታወቅ ይህን ያህል ጊዜ የፈጀበት አገር ቢኖር ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሳትሆን አትቀርም። እንደሚታወሰው ምርጫው በተካሄደ በማግስቱ አቶ መለስ ለመግዛት የሚያስችለኝ ሶስት መቶ የፓርላሜንት መቀመጫ አግኝቻለሁ ብለው ለፈለፉ። የምርጫውን ቆጠራና ውጤት ማሳወቅ የብሄራዊ ቦርዱ ኃላፊነትና ተግባር መሆኑ እየታወቀ አቶ መለስ ቸኩለው ፓርቲዬ በአሸናፊነት ወጥቷል ማለታቸው አምባገነን ባህርይ የተዋሃዳቸውና ከመጀመሪያውኑ መሸነፋቸውን አውቀው ህዝብን ለማወናበድ ያደረጉት እርምጃ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ የአቶ መለስ ልፈፋ ከምርጫ ቦርዱ በኩል አልግባብ መሆኑን ግሰጻ መሰንዘርና የምርጫውን የቆጠራ ሂደት የሚያደናቅፍና መገታት ያለበት መሆኑን ማመልከት ሲገባ ፣ የምርጫ ቦርዱ ይህንን የአቶ መለሰን ልፈፋ ለማረጋገጥ ራሱ የድምጹን ቆጠራ ለገዢው ፓርቲ በሚያመች መልክ እን ዲካሄድ አደረገ። ራሱ በብሄራዊ የምርጫ ቦርዱ የወጡ የድምጽ ቆጠራ ውጤቶች እንደ ሚያረጋግጡት ፣ 1ኛ) ካለምንም ገለጻ ለመምረጥ የተመዘገቡት ሰዎች ቁጥር ተለወጠ 2ኛ) በአንዳንድ ቦታዎች ለመምረጥ ድምጻቸውን የሰጡት ሰዎች ቁጥር ከሚገባው በላይ ሆነ ወይም ደግሞ በፍጹም መማን የሚያስችል አይደለም 3ኛ) በደምጽ ቆጠራው ሂደት ውሰጥ የተሰጡት ድምጾች ለኢህአዴግ እንዲያመች ሆነው ተቆጠሩ። በዚህ መልክ የምርጫ ቦርዱ ወገናዊ መሆኑን ያረጋገጠና በህግ የተረጋገጠለትን መመሪያ ይዞ በሱ መንፈስ የምርጫውን ቆጠራ ሊያካሂድ በፍጹም አልቻለም። በየጊዜው እየትዝረክረኩ የሚወጡት ውጤቶች በሙሉ ወያኔ/ ኢህአዴግ እንዳሸነፈ ሆኖ ነው ይቀርብ የነበረው። ይህንን በሚመለከት የአውሮፓው አንድነት ተጠሪ የሁኑ የምርጫው ተመልካቾችና ውጤቱን የሚቆጣጠሩት ፣ የምርጫው ቆጠራ ሂደት እንዳለስደሰታቸው ከአንዴም ሁለቴም አረጋግጠዋል። ይሁንና ከሰኔ 1 እልቂት በኋላ በአውሮፓው ልዑካን አስታራቂነት የምርጫው ሂደት ተዛብቶባቸዋል በሚባልባቸው ቦታዎች በሙሉ እንደገና እንዲቆጠር በቅንጅትና በኢህአዴግ መሀከል ስምምነት ቢደረስም የምርጫ ቦርዱም ሆነ የኢህአዴግ ካድሬዎች ሂደቱን ለማጨናገፍ ፣ የማባረር ፣ የማፈንና የግድያ ከዚያም አልፎ ግልጽ የድምጽ መስረቅ ውስጥ ነው የገቡት። ኢህአዴግን እልክ ለማሰጨረስ በማጣራቱ ሂደት ቢገፋበትም ከውጭ በመጣውም ግፊት ሆነ ካላግባብ ህጋዊ መስመሮችን መጠቀም ያስፈልጋል በሚለው አቋም ብዙ የፖለቲካ ስህተቶች ተሰርተዋል። ይህንን በሚመለከት አቶ ልደቱም ሆነ የቅንጅቱ ሊቀመንበር አቶ ኃይሉ ሻውል ሰፋ ያለ ገለጻና የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ኢህአዴግን ለጊዜውም ቢሆን የፖለቲካ ሜዳውን እንደልቡ እንዲጋልብበት በር እንደከፈተለት አረጋግጠዋል። ከዚህ በተረፈ ምን እናድርግ? በሚል በአዲስ አበባ ውስጥ ጥቂት ግለሰቦችን ጠርቶ ማወያየት ለምርጫው ውጤት ሌላ ውዥንብር እንዳከለበት ይታወቃል። በኋላ ይህ ጉዳይ በአሰቸኳይ እንዲታረምና አቶ ኃይሉ ሻውል በሰጡት አመርቂ ትንተና ሊታረም ችሏል። እዚህ ላይ አቶ ኃይሉ ሻውል የወሰዱት ትክክለኛ እርምጃና የሰጡት ትንተና የውጭ ኃይሎች ፣ በተለይም ደግሞ አሜሪካ ለመሞት በጣር ላይ ለሚገኘው የወያኔ/ኤህአዴግ አገዛዝ ነፍስ ለመዝራት እንደሚሯሯጡና የአገራችንን ድህነት ለማራዘም የማይሸርቡት ተንኩል እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል። የማያስፈልግ ፣ በውጭ ኃይሎች የተደረገው መተማመን ከፍተኛ ስህተት መሰራቱን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ህዝቡ የሚመኘውን ዲሞክራሲያዊ ህይወትና አገርን በጋራ የመገንባት ፍላጎት እንደሚያጨናግፈው ለብዙዎች ግልጽ አልነበረም። አይደለምም። በተለይም ይህ በአ.አ በ1980 ዎች ውሰጥ በአንዳንድ የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች የፈለቀው የውጭ ኃይሎችን በሬል ፖለቲካ ስልት እናሳምናለን የሚለው አጉል ዘይቤ ወደ አንዳንዶችም ጋር በመዛመቱ ትክክለኛና ቆራጥ ርምጃ እንዳይወስዱ አግዷል። እነዚህ የሬል ፖለቲካ ዘይቤና የዲፕሎማሲ ትግል የተናወጣቸው ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ትግሉን ከማቀዝቀዛቸውም ባሻገር ፣ ለግዜውም ቢሆን ኃይል እንዲበታተንና ብዙ ሰውም እንዲጠቃ

ሁኔታውን በተጨባጭ ለኢህአዴግ አመቻችተዋል ማለት ይቻላል። ምዕራብ አውሮፓም ሆነ አሜሪካ ሬል ፖለቲካ ሲሉ እነሱ በሚፈልጉት መንገድ የድሀ ህዝቦችን ትግልና ዕድል ለመጠምዘዝና የድህነቱን ዘመን ለማራዘም እንጂ ዕውነተኛ ዲሞክራሲያ ህይወት በአገራችን ምድር እንዲያብብ ለማድረግ አይደለም። በታሪክም ታይቶ አይታወቅም። በተለይም በአሁኑ ወቅት ከፖለቲካ ጥራት ይልቅ የፖለቲካ ኮክቴል በበዛበት ሁኔታ ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦች በዚህም በዚያም ብለው ጥራት ካለው ውይይት ይልቅ ንግግራቸውን በተወሰኑና "ምራቅ በዋጠ አነጋገር" እየሸፋፈኑ ለስልጣኔና ለዕውነተኛ ነፃነት የሚደረገውን ትግል እን ደሚያጨናግፋ መታወቅ አለበት። በሌላ ወገን ግን ዲፕሎማሲዊ ትግል በፍጹም አያስፈልገም ማለት አይደለም። ዲፕሎማሲያዊ ትግልም ማካሄድ የሚቻለው ውስጣዊ ጥንካሬ ሲኖር ብቻ ነው። በውጭ ርዳታ ተመጽዋች የሆነች አገር ለሷ የሚያመቻትን የዲፕሎማሲ ትግል ለማካሄድ እንደሚያስችግራት በግልጽ መታወቅ አለበት።የዲፕሎማሲ ትግልም የሚካሄድ ከሆነ ፣ የትግል ስልቱ የአገራችንን ነፃነትና ዲሞክራሲያዊ ግንባታ በማያሰተጓጉል መልክ መካሄድ አለበት። አንዳንድ ግለሰቦች እንደፈለጉ እንዳይዋኙ የፓርቲ ቀጥጥርና ስርዓት የተከተለ ግኑኝነት እንዲመሰረት በየጊዜው የዓለም ሁኔታ መገምገም አለበት። ግለሰቦች ብቻቸውን ስህተት ይሰራሉ። በተለይም በአገራችን ገና ዲሞክራሲያዊና የትችት ባህል ባልዳበረበት ሁኔታ ውስጥ ኃላፊነትን ለአንዳንድ ግለሰቦች መሰጠት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። አውሮፓ ውስጥ እንደምናየው የፖለቲካ መሪዎች ብዙ አማካሪዎች አሏቸው። መሪዎች የሚወስዷቸው ርምጃዎች በሙሉ ተፍተልትለውና በበቂው ተተንትነው ነው። ስለዚህም በአገራችንም ይህ የአሰራር ዘዴ መለመድ አለበት። ዲሞክራሲም ሊያብብ የሚችለው በዚህ መልክ ብቻ ነው።

ወደ ሌላው ነጥብ እንምጣ። ሰሞኑን የተያዘው ፈሊጥ ደግሞ ከኢህአዴግ ጋር አን ዳች ዐይነት መንግስት መስርቶ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ህዝባችንን ለሌላ ምርጫ ማዘጋጀት ይቻላል የሚለው አደናጋሪ መፈክር ነው። ይህ ሀሳብ ትክክል የሚሆነው ወያኔ ትንሽም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ ባህል ያለውና ለመደራደርም ፈቃደኛ የሆነ ቢሆን ነበር። በአስራ አራት ዐመት የተመክሮና የሽሩሩ ፖለቲካ የወያኔ መሪዎች አንዳችም የተማሩት ነገር የለም። ከ በምርጫው ማግስትም የወያኔ መሪዎች ለምን ተሸነፍን ? ለምን ህዝቡ ከዳን ? ብለው ከመጠየቅ ይልቅ በየክፍለ ሀገሩ ለምን አልመረጥከኝም እያሉ ነው ህዝቡን ማዋከብ የገቡት። ህዝቡ ህክምና ፣ ዘርና ማዳበሪያ ሲጠይቅ የመረጥካቸውን ቅንጅትና ህብረት ይስጡህ እያሉ ነው ማባረር የጀመሩት። በሌላ በኩል ቅንጅትና ህብረት ስልጣን ቢጨብጡ የወያኔን ካድሬዎችንም ሆነ ኢህአዴግን የመረጠውን ክፍል ሂዱና ወያኔ ርዳታ ይስጣችሁ ብለው መብታቸውን ሊነፍጓቸው በፍጹም አይችሉም። ዕምነታቸውንና መብታቸውን ስለገለጹና ስለተጠቀሙ ፍዳ የሚያዩበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም። በኢህአዴግና በካድሬዎቹ አመለከከት ግን ጊዜያዊ ጥቅም ከዕምነትና ከህሊና ነፃነት መቅደም አለበት። ስለዚህም እሱን የማይፈልግ ፍዳውን ማየት አለበት። በዚህ ዐይነት ስንቶች ተሰቃዩ። ስን ቶቹ ተሰደዱ። ከምርጫው በኋላ የተፈጸሙት ድርጊቶች በሙሉ የሚያረጋግጡት አገዛዙ በምንም ዐይነት ስልጣኑን ላለመልቀቅና የህዝባችንን ሰቆቃ ለማራዘም ቆርጦ እንደተነሳ ነው። ከዚህም በላይ አስራ አራት ዐመት ያህል ያካበታቸው ህብቶች ፣ እርስ በርሱ የተሳሰረ የእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካና ማፊያዊ ተግባር እንዳይፈራረስበት ይፈልጋል። ይህንንም በሚመለከት አቶ መለስ በቂ መቀመጫ እንዳለቸውና የጣምራ መንግስትም ማቋቋም ህገ-መን ግስቱን እንደሚፃረር በማያዋላዳ ቋንቋ ተናግረዋል። በተጨማሪም ውስጥም ሆነ ውጭ ሆኖ የሚቃወማቸውን ኃይል በሬዲዮ ፋና በሰጡት ቃለ-ምልልስ በእሳት እንደሚፈጇቸው አረጋግጠዋል። ለጦርነት የተዘጋጁ መሆናቸውን ከአንዴም ሁለቴም ተናግረዋል። ታዲያ ይህ ግልጽ እየሆነ የሽግግር መንግስት እናቋቁም የሚለው መፈክር ህዝቡን የሚያደናግር አይሆን ም ወይ ? በሌላ ወገን ደግሞ አንዳች ዐይነት የጣምራ ወይም የሽግግር መንግስት ቢቋቋም ማነው የበላይነቱን የሚይዘውና ሁኔታውን ለሌላ ምርጫ የሚያዘጋጀው ? በወያኔ ቁጥጥር ስር ያሉ ማፈኛ መሳሪዎች ፣ የፀጥታና የስለላ ኃይሎችስ በማን ቁጥጥር ስር ይውላሉ ? በሂደቱ ውስጥ ኢህአዴግ አደጋ ቢያደርስስ ? ላለማድረስ ምን ዋስትና ይኖራል ? ኢህአዴግ በኢኮኖሚው ላይ ያለውስ ቁጥጥር እንዴት ሊታይ ይችላል ? እነዚህና ሌለች የተወሳሰቡ ሁኔ

ታዎችን ስንገመግም ሁኔታው ለሽግግር መንግስት የሚያመች አይደለም። እንዲያውም እን ደዚህ ዐይነቱ ሙከራ የህዝባችንን ምኞት ለብዙ ዐመታት ተንጠልጥሎ እንዲቆይ የሚያደርግና የረሀቡንና የድህነቱን ዘመን የሚያራዝም ነው። ለስትራቴጀ ተብሎ ካለሆን በስተቀር ከኢህአዴግ ግትርና አደገኛ ፖለቲካ አኳያ ስንገመግመው ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አይደለም። ህዝባችን በግንቦት ስምንት ድምፁን ሲሰጥና ቅንጅትንና ህብረትን በብዙ ድምጽ ሲመርጥ በማያወላውል መልኩ ያሰመሰከረው ዕውነተኛ የአገዛዝ ለውጥና ዲሞክራሲዊ ህይወት እየተዋሃደው አዲስ ኢትዮጵያን ለመገንባት ነው። ከላይ እንዳልኩት የግንቦት ስምንቱ ምርጫ ተራ ምርጫ አይደለም። መሰረታዊ ለውጥ እንዲካሄድ የጋበዘ ሌላው የካቲት ነው ማለት ይቻላል። የአገዛዙን የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የስለላ መሰረት በደምሰስ የሰለጠነችና የተከበረች ኢትዮጵያን ለመገንባት የተደረገ ሰፊ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ነው። ሰሞኑን የተከሰተው የፖለቲካ ሁኔታ ደግሞ ይበልጥ የሚያደፋፍረንና ኢህአዴግን በውስጥም ሆነ በውጭ የፖለቲካ ተከላካይነት ውስጥ እንዲወድቅ ያደረገ ሁኔታ ነው። አገዛዙ ክፉኛ አጣብቂኝ ውስጥ የገባና በየጊዜው ስህተት እየሰራ የሚሄድ ነው።

ስለዚህም የኛ ትግል ይህንን የህዝባችንን ፍላጎትና የመጪውንም ትውልድ ዕድልና ህይወት የሚመለከት መሆን አለበት። ትግሉ አዲስ ኢትዮጵያን በፀና መሰረት ላይ ለመገን ባትና በዚያች ምድር ላይ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በጋራና በመከባበር ሊኖር የሚችልባትን አገር አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ነው። ሳይንስና ቴክኖሎጂ አብበው ህዝቡ ከጨለማ ኑሮ እን ዲላቀቅ ማድረግ ነው። የህዝባችንን የኑሮ ሁኔታ በየጊዜው እያሻሻሉ እርግጠኝነት እየተሰማው ታሪክን ሰርቶ ለመጪው ትውልድ እንዲያስተላለፍ ነው። ትግላችን የተወሳሰበ ነው ማለት ነው። የትግላችንም ጥራት መኖርና አለመኖር ፣ በትንሽ ነገሮች ተደስቶ እጅን አጣጥፎ መቀመጥና ያለመቀመጥ ወደፊት በምናደርገው ሂደት ውስጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣል። በዚህ መሰረት የሚጠበቅብን ኃላፊነት ከባድ ነው። ምናልባት አንዳንዶቻችን ልን ሸከመው አንችልም። ሌሎቻችን ደግሞ ትክክለኛውን የትግል ፈለግ ይዘን እንጓዝ ይሆናል። የትኛው መንገድ በአሸናፊነት እንደሚወጣ በእርግጥ መናገር ባይታወቅም አንዳንድ ቦታዎችና አንዳንድ ግለሰቦች ጋ በግልጽ እንደሚታየው የሴንሴሽን ፖለቲካ እየገፋ መጥቷል። ትግላችን በሰፊ የሳይንሳዊ መሰረት ላይ ከመመርኮዝ ይልቅ ወሬዎችና አሉባልታዎች አይለው ይገኛሉ። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ መወያየት ያለብን ብዙ ቁም ነገሮች አሉ። በአገራችን ጎልቶ የሚታየውን ረሀብና ድህነት እንዴት ልናጠፋው እንችላለን ? በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሰፊው ህዝብ መልስ የሚሰጥና ተስፋ የማያስቆርጥ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዴትና በምን መልክ መከተል እንችላለን? በአገራችን ምድር እንደ ደቡብ አፍሪቃ ፣ ናይጀሪያ ፣ ኬንያና ብራዚል ተስፋ የመቁረጥ መንፈስ እንዳይታይ ምን ምን እርምጃዎችን መከተልና መውሰድ እንችላለን ? ከውጭ የሚመጣውን የአነ አይ ኤም ኤፍንና የዓለም ባንክን ግፊት እንዴት መቋቋም እን ችላለን ? የነሱን ቲዎሪ ለመቋቋም የምንችልበት የራሳችን የሆነ የቲዎሪ መሳሪያ አለን ወይ ? ከውስጥ ሀብት እንዴት እናዳብራልን ? የህዝቡን የተዝረከረከ ኑሮ መሰመርና ስርዓት እን ዲኖረው ለማድረግ በየትኛው የህብረተሰብ ፍልስፍና መመራት አለብን? እነዚህን የመሳሰሉትን ና ሌሎችንም ጥያቄዎች እያነሳን ለመወያየት ለጊዜው ገቱ ያለ አይመስልም። አሁን ካለን በት የሴንሴሽናል ፖለቲካ ካልተላቀቅንና የዓለምን የተወሳሰበ ፖለቲካ እያጠናን ወደ ውጭ ወጥተን ካልተወያየንና ህዝቡን ካላስተማርን የህዝባችን ትግል ተጨናግፎ እንዲቀር አስተዋጽዎ አደረግን ማለት ነው። ስለዚህም እያንዳንዳችን በራሳችን ላይ በመተማመን ከመሪዎች የሚመጡትን ገለጻዎችም ሆነ የፖለቲካ ርምጃዎች ለመገምገም ከፍተኛ የጭን ቅላት ስራ መስራት መቻል አለብን። ይህ ግልጽ አስካልሆነ ድረስና ዕምነታችንን በጥቂት ሰዎች ላይ ጥለን የጭፍን ጉዞ የምንጓዝ ከሆነ ከአምስት ዐመት በኋላም ለዚህ ነበር ወይ? የታገልነው ብለን ራሳችንን መጠየቃችን አይቀርም።

ከዚህ ስንነሳ የቅንጅት መሪዎች ለአባሎቻቸው ፣ በተለይም ደግሞ በንቃት ለሚሳተፉት ትግሉ በምን መልክ መካሄድ እንዳለበት መመሪያ መስጠት አለባቸው። አገራችን ታሪክ የሚሰራባት መሆኑን ተገንዝበው ሰፊ የቲዎሪ መመሪያዎች በማዳበር በአባሎቻቸው መንፈስ

ውስጥ ሰርጎ እንዲገባ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አለባቸው። በአንዳንድ አካባቢ የሚታየው ለዘብ ያለ አመለካከት በጊዜው ካልታረመ ትግሉ የፈለገውን ግብ ሊመታ አይችልም።

የምርጫውን ውጤት በሚመለከት የብሄራዊ ምርጫ ቦርዱም ሆነ ወያኔ/ኢህአዴግ አሸነፍኩ ቢሉምና አንዳንድ መንግስታትም የኢህአዴግን ማሸነፍ በደስታ ቢገልጹ ፣ የትም የሚያደርሰቸው አይደለም። አሁን ይህ ጽሁፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ የናይጀሪያ መንግስት ለኢህአዴግ ድሰታውን ገልጿል። የአይጥ ምስክር ድንቢጥ እንደሚሉት ዐይነት ነው። የፕሬዚደንት ኦቦሳንጆ አገዛዝ በስድስት ዐመት ውስጥ ምንም ዐይነት ለውጥ ለናይጀርያ ህዝብ እንዳላመጣ ይታወቃል። የናይጀሪያ ህዝብ ስንትና ስንት ሀብት እያለው ይህንን ሀብት ለአገሩ ዕድገት መጠቀም ያልቻለ መንግስትና አገሪቱን የመልቲ ናሽናል ኩባንያዎች መፈንጫ ያደረገ አገዛዝ እንደ ኢህአዴግ ያለውን አገዛዝ ደስታውን ቢገልጽለት ሊደንቀን አይገባም። ስለዚህም የኛ ትግል በዚህ ሳይደናበር የህዛባችን ድምጽ እንዲከበርና ዲሞክራሲያዊ ሰርዓት እንዲገነባ ያልቆጠበ ትግል ማድረግ ነው። በምንም ዐይነት የግንቦት ሰምንቱ ምርጫና ውጤት ተድበስብሶ መቅረት የለበትም። በሌላ በኩል አንዳንድ ዲሞክራት እየመሰሉ የማያስፈልግ ጽሁፍ የሚጽፉና ህዝብን የሚያደናብሩ ግለሰቦች መቆጠብ መቻል አለባቸው። አንዳንድ ጽሁፎች ከመጀመሪያውኑ ሲመለከቷቸው ውስብስብና ትክክለኛ መስለው ሊታዩ ይችላሉ። በደንብ መስመር ለመስመር እየተነተኑ ሲነበቡ ትግሉን የሚያዘናጉና የኢህአዴግን ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ዘመን የሚያራዝሙ ናቸው። ጽሁፎች ለመጻፍ ተብለው መጻፍ የለባቸውም። ትክክለኛ መልዕከት የያዙና የህዝብን ትግል የማያዘናጉ ሆነው መቅረብ አለባቸው። በተጨማሪም በግልጽ ቋንቋ መቀመጥ አለባቸው። ከዚህ ባሻገር ወደድንም ጠላን ም እያንዳንዳችን የራሳችን የፖለቲካ መመሪያና ዕሴት አለን። እንዲሁም ለኢትዮጵያ የየራሳችን ርዕይ አለን። ጽሁፎችን በአጠቃላይና በአደናጋሪ መልክ ከማስቀመጥ ይልቅ ለየትኛይቱ ኢትዮጵያና ምን መምሰል እንዳለባት በግልጽ ማስቀመጥ አለብን። ዕምነታችንን ወደ ፊት ማውጣት አለብን። የቲዎሪ ጥራት ሳይኖረው በጥሩ ቋንቋ የሚቀርብ ጽሁፍ ሶፊዝም ነው። ወደ ዕውነተኛ ነፃነት አያመራም። የስልጣኔውን ጎዳና አያመለክትም። በአንፃሩ አድበስብሶ በማስቀመጥ የጨለማውን ዘመን የሚያራዝም ነው። ስለዚህ በአንድ በኩል ትግላችንን እያሟሟቅን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በማያሻማ መልኩ ለየትኛይቱ ኢትዮጵያ እን ደምንታገል አቋማችንን በግልጽ ማሳየት አለብን። ካለበለዚያ ትግላችን አደባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንደሚባለው አነጋገር ይሆናል ማለት ነው።

ፈቃዱ በቀለ/ከበርሊን